# እውነት መንፈሳዊ ጋዜጣ



እንኳን 2010 ዓ.ም እ/ር በሰላም አደረሳችሁ!!

# በውስጥ ገጾች

❖ **ዕርሰ አንቀጽ፤**

- **እግዚአብሔር ክብሩንያሳየን**

❖ ***ምስክርነት፤***

**ገንዘብ ቤት ጥሩ ስራ ወይም ቤተሰብ እና ብዙ ወዳጆች በዙሪያችን ስላሉ ትዳር እንደቀላል እመሰርታለሁ ማለት እንደማይቻል እኔ በህይወት አይቻለሁ**

❖ **የትምህርት ዓምድ፤**

- ***ቅብብሎሽ***

  **ቤተ-ክርስቲያን ከራሷ ሓኪም ከጌታዋ ካልተጣበቀች ስም አንጠልጥሎ ከመኖር ያለፈ ነገር ሊኖራት አይችልም!**

❖ ***መጣጥፍ***

- **ሳይገኙ መገኘት**

  **በእግዚአብሄር ሕዝብ ፊት ለመገኘት አስቀድሞ በእግዚአብሄር ፊት መገኘት የግድ ይላል!**

- **የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን**

  **ክርስቲያኖች ሁል ጊዜ በዚህ ምድር ስንኖር ከሌሎች የሚለየን አንዱና ዋነኛው ነገር የተሰቀለውን ክርስቶስን መስበካችን ነው**

❖ ***የግጥም መድብል***

- **ሕዝብ ይረፍባችሁ**

  **እረኛ ነኝ ብሎ ሰይሞ እራሱን**
  **ካሉት ምዕመናን አያውቅም አስሩን**




**በቦስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የምታምን የክርስቶስ ኢየሱስን የማዳን ወንጌል ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የምታሰራጭ ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህም ጋዜጣ ወንጌልን ከምታሰራጭባቸው መንገዶች አንዱ ሲሆን በቤተ ክርስቲያን የሥነ-ጽሁፍ አገልግሎት አባላት እየተዘጋጀ በየሁለት ወር አንድ ጊዜ ይቀርባል።**

**የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ**
**ፓስተር ምሕረቱ ሌጂቦ**

Email: Meheretu2614@yahoo.com
Telephone: 617-792-5764

**ዋና አዘጋጅ ..........ሄኖክ ተሾመ**
**ምክትል አዘጋጅ........ ሐብታሙ አሰረስ**
**የውብዳር ፍሰሐ**
**ኮምፒዩተር ጽሑፍ... . ትርሲት ጥላሁን**
**የፊት ገጽ ዲዛይነር...የዝግጂት ክፍሉ**

**ለቀጣዩ እትም ይረዳ ዘንድ የእናንተ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ስላለው በሚቀጥለው አድራሻ ያላችሁን አስተያየትና ጥያቄ ላኩልን። አድራሻ:**

Ethiopian Evangelical Church in Boston
88 Tremont Street
Boston, MA 02108
Tel. 617-816-8827
E-mail: Henokekka@yahoo.com

# ርዕሰ አንቀጽ፤

## እግዚአብሄር ክብሩን ያሳየን

የእግዚአብሄር ክብር በሕይወታችን በቤተ-ክርስቲያናችን ብሎም በምድር ሁሉ ባለችው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንዲገለጥ እጅግ እንጓጓለን ፡፡ በዚህ አቅጣጫ መልስ እንዲያመጣልን ንስሃ በመግባት በጾም ጸሎትም ደጅን እንጠናለን ነገር ግን ቆም ብለን ክብርህን አሳየን ስንል ክብርህ በመካከላችን ይገለጥ ስንል ምን ማለታችን ነው ? ምንስ እንዲሆን ነው የፈለግነው ብለን እራሳችችንን የምንጠይቅበት ጊዜ አለ? እንግዲህ የሚመራንን ክቡር የሆነውን የእግዚአብሄርን ቃል እና ባለፉት ዓመታት የሆነውን የቤተክርሥቲያንን ታሪክ ስንመለከት እግዚአብሔር ክብሩን እየገለጠ ከሁሉ የበለጠ የእርሱ ስም ከብሯል ሰዎች ደግሞ ተጠቃሚ ሆነዋል። የእግዚአብሄር ክብር መገለጥ ማለት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተገለጠ መልኩ መስራት፤ የጌታ የኢየሱስ ስሙ እጅግ ከፍ ማለት፤ የሰዎች ልብ ለእግዚአብሄር ተከፍቶ በብርቱ ጥማትና ረሃብ እግዚአብሄርን ከልብ መፈለግ ፤ሁሉም ሰው ስለ ኀጢአቱ ተጸፅቶ በተሰበረ ልብ በእንባ ንስሓ በመግባትና ከህሊና ክስ ነጻ ሆኖ ማረፍ፤ ለጽድቅና ዘላቂነት ያለው የድል ሕይወት ወንጌሉን ለጠፋበት ለማድረስ ድፍረትና ኃይል ማግኘት፤ በትጋት የመንግስቱን ስራ ለመስራት መነሳት፤ ያለግብዝነት በእውነተኛ ፍቅር ቅዱሳንን ሁሉ ያለ አድልዎ መውደድ፤ ለጸሎት አብሮ መትጋት፤ እውነተኛና ከውስጥ የሆነ አድናቆት በተሞላ መልኩ አምልኮን ለእግዚአብሔር ማቅረብ ፤የሰዎች ከኀጢአት ሰንሰለት ነጻ መውጣት፤ ለክርስቶስ ተማርከው ወደቤቱ የሚመጡ ሰዎች ቁጥር መብዛት፤ የጸጋ ስጦታዎች በተገለጡ መልክ መስራት እና ሰዎች ከአጋንንት እስራት  መላቀቅ ሲሆኑ ቃሉ በስልጣንና በኃይል ይሰራል ሰው ሁሉ ለቃሉ ምላሽ ይሰጣል

እግዚአብሄርን መፍራት በሰው ሁሉ ላይ ይታያል እንግዲህ የእግዚአብር ክብር በመካከላችን ሲገለጥ ከዚህም ያልፈና የበለጠ ነገር በቤተክርስቲያን ይሆናል ብዙ መንፈዊ ጥያቄዎቻችን መልስ ያገኛሉ እግዚአብሄር ክብሩ በግል ህይወታችን እና  በቤተክርስቲያናችን እንዲገለጥ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ፊቱን በብርቱ በመፈለግ እንትጋ ተግተው የሚፈልጉት ያገኙታልና እባክህን ክብርህን አሳየን በማለት አምላካችንን እንማጸነው::

*የቤተ ክርስቲያኒቱ መልዕክት*



# የቤተሰብ ዓምድ

***ምስክርነት**.......*

*የእህት መቅደስን ሰፋ ያለ የሕይወት ምስክርነት ባለፉት ሁለት እትማችን ላይ  አቅርበንላችሁ ነበር። ዛሬ ደግሞ የመጨረሻ የሆነውን ስለ ትዳር ሕይወታና ሰለ አገልግሎታ ከባለቤታ ከወንድም በላይ ጋር የሰጡንን ምስክርነት ይዘን ቀርበናል።*

***እውነት፦** በመጀመሪያ ስለ ትዳር ሕይወታችሁ እና ሰለ አገልግሎታችሁ ያላችሁን የሕይወት ምስክርነት ልትሰጡን ፈቃደኛ በመሆናችሁ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን ጌታ ይባርካችሁ።*

*ዛሬ ቅድሚያውን ለወንድም በላይ እንስጣለን። መቅደስን የትዳር ጋደኛ እንድትሆን ስትመርጣት ምክንያትህ ምን ነበር?*

***በላይ ፦** መቅዲ የትንሿ እህቴ ጓደኛ ነበረች። ከዚያም አልፎ በቤተሰብ ደረጃ |እንተዋወቅ ነበር። ታዲያ ከነበራት መልከ መልካምነት በተጨማሪ የነበራት ስነምግባር እና መንፈሳዊ ሕይወት እጅግ ይማርከኝ ነበር። በእነዚህ ምክንያቶች ነበር ለትዳር ጋደኝነት የመረጥካት።*

***እውነት፦** መቅደስ የጋብቻ ጥያቄውን በምን መልኩ ተቀበልሽው?*

***መቅደስ፦** በጣም ነው የደነገጥኩት ምክንያቱም ከእርሱ የማልጠብቀው ጥያቄ ስለነበር እኔ ልክ እንደወንድሜ አድርጌ ነበር የማየው*

***እውነት፦** እኮ ምላሽሽ ምን ነበር?*

***መቅደስ፦** እኔን እንደእህትህ አስበኝ እንዲህ አይነት ነገር ከልብህ አውጣ አልኩት።*

***እውነት፦** ጥያቄህን እንዳልተቀበለች ስታውቅ ምን አደረክ?*

***በላይ፦** በወቅቱ ወደ አሜሪካ ለመምጣት ዝግጅቴን ጨርሼ ስልነበር ወደ አሜሪካ መጣሁ ሆኖም ጉዳዬን በደብዳቤ ቀጠልኩ እሷ ግን ፈቃደኛ አልነበረችም። ከዚህ በኋላ እንድጸልይልህ የምትፈልገው የጸሎት ርእስ ከሌለህ በስተቀር ደብዳቤ እንዳትጽፍልኝ እንዲህ አይነቱንም ሀሳብ ከልብህ አውጣው አለችኝ።*

***እውነት፦** ታዲያ ዳግም እንዴት ተገናኛችሁ?*

***በላይ፦** ጊዜውን በትክክል አላስታውሰውም ይህንኑ ጥያቄ በድጋሚ አቀረብኩላት............*

***እውነት፦** አሁንስ ያንች ምላሽ ምን ነበር?*

***መቅደስ፦** የሚገርም ነገር ነው የሆነው እኔ በጌታ ፊት ለ15 ቀናት ጊዜ ወስጄ በትዳርም አቅጣጫ ፈቃድህን አሳውቀኝ እያልኩ ስጸልይ ቆይቼ ስናነሳ የእርሱ ደብዳቤ ደረሰኝ በስአቱ ስላልገባኝ እንዴ ይሄ ሰውዬ እስካሁን ድረስ አላገባም ? ብዬ እራሴን ጠየኩ አሁንስ ዝም እለዋለሁ ብዬ ሳስብ ጌታ በምረዳው በሚገባኝ መንገድ ብዙ ጊዜ ተናገረኝ ከዚያ ቆም ብዬ አስብኩና እንደገና ጌታ እንዲረዳኝ ለመንኩት ከዚያም የጌታን ፍቃድ ስላውቅሁ አመስግኜ ጥያቄውን መቀበሌን የሚገልጽ ደብዳቤ ላኩለት ከዚያ ቦኋላ ጉዞ ጀመርን።*

***እውነት፦** የብዙ ያላገቡ ክርስቲያኖች ጥያቄ ወደ ትዳር አለም ከመግባታችን በፊት የእግ/ርን ፈቃድ የምናውቀው እንዴት ነው? የሚል ነው እናንተ ደግሞ ከመተዋወቅ አልፋችሁ ትዳር መስርታችሃል ለሌሎች ትምህርት ይሆን ዘንድ ጋብቻችሁ በእግ/ር ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ለመሆኑ ያረጋገጣችሁት በምንድን ነው?*



*( እህት ምቅደስና ቤተሰቦቿ)*

***በላይ፦** እኔ ብዙ የምናገረው የለኝም ነገር ግን ትዳሬ በእግ/ር ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ለመሆኑ አንዳች ጥርጥር የለኝም። ምክንያቱም በራሴ የተራመድኩትን የስህተት መንገድ እስኪገባኝ ድረስ እግ/ር እራሱ እየዘጋው ፈቃዱ ያለበትን ይህን የተባረከ ትዳር በተአምራት አሳልፎ በእጄ ስጥቶኛል። ገንዘብ ቤት ጥሩ ስራ ወይም ብዙ ቤተሰብና ወዳጅ በዙሪያህ ስላሉ ትዳርን እንደቀላል እመሰርታለሁ ማለት እንደማይቻል እኔ በህይወቴ አይቻለሁ። ጥያቄውን በቀጥታ ለመመለስ ከመቅዲ ጋር ለመጋባት ሳስብ የውሰጥ ሰላም ነበረኝ ደግሞ እወዳታለሁ ።*

***መቅደስ፦** እኔ ከላይ እንደተናገርኩት የእግ/ርን ፈቃድ ያረጋገጥኩበት መንገዶች ብዙ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት በቃሉ እንዲሁም ጌታ ለራሴ በሚገባኝ መንገድ ተናግሮኝ ነው። እግ/ር ይመስገን ሌላው ሰው የእግ/ርን ፈቃድ ማውቅ ከፈለገ ልቡን ለጌታ ክፍት አድርጎ ተግቶ መጸለይ ነው ለሁሉም በሚገባን መንገድ ይናገረናል።*

***እውነት፦** በእጮኝነት ጉዞ ከጀመራችሁ በኋላ ግንኙነታችሁ ተቋጥሮ ነበር። ምክንያቱ ምንድ ነው?*

***በላይ፦** ችግሩ የነበረው እኔጋ ነው። እርሷ ለስማችዉ እውነት ጸንታ ቆማለች እኔ ግን አልቻልኩም እርሷን ወደ እዚህ ( አሜሪካ) ለማስመጣት በብዙ መንገድ ሞከርኩኝ አልተቻለም በሮች ሁሉ ተዘጉ ...*

*ወደ ገጽ 6 ዞራል*

## መጣጥፍ

### ሳይገኙ መገኘት ለምን ?

የዛሬ ጽሑፌን በአባቶቻችን አባባል ልጀምር "ያልሰማ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል" ቃሉ ምንም መንፈሳዊ ባይሆን ዘረፈ ብዙ መልዕክት አለው ጸብ ውስጥ እንዳትገባ ፤ እንዳትሳሳት፤ አላዋቂ ተናጋሪ እንዳትሆን የሚሉ ተዛማች ትርጉሞችን የያዘ ነው እኔም ዛሬ ተመሳሳይ ትርጉም የያዘ ሳይገኙ መገኘት ለምን? በሚል ርዕስ መጣጥፌን ይዤ ቀረቢያለሁ…

በእግዚአብሔር ሕዝብ ፊት ለመገኘት አስቀድሞ በእግዚአብሔር ፊት መገኘት የግድ ይላል! በእግዚአብሔር ፊት ሳንገኝ በሕዝቡ ፊት መገኘታችን ለምን? ምንስ ልንል ይሆን?

ያልተነገረንን ልንናገር ያልሰማነውን ልናሰማ?ይህ ደግሞ ጸቡን የሁለትዮሽ ያደርግብናል። አንደኛው ያላለውን ስንል ይህንን ከየት አመጣኸው እኔ አልነገርኩህም በሚል ከፈጣሪ ጋር ሲያጋጨን ሁለተኛው ደግሞ ከአምላኩ ዘንድ ያልሆነ መል ዕክት የደረሰው ህዝብ ነገሩ ከላይ እንዳልሆነ ሲገባው ምነው ከኪስህ አውጥተህ ትናገራለህ በሚል ጸብ ይፈጥራል። ልብ በሉ በ እግዚአብሔር ፊት ተገኝተን ስሜታችንን እያዳመጥን ማገልገል እንጀምራለን ይህ ደግሞ ከባድ አደጋ ነው።

እኛ አገልጋዮች በእግዚአብሔር ፊት ጊዜ ወስደን ፤ ተንበርክከን ጸልየን፤ቃሉን አንብበን እና ለሕዝቤ የምትናገረው ይህ ነው ተብለን ስንመጣ በመድረክም ፍሬ ያለው አገልግሎት እንሰጣለን ነገር ግን በፊቱ ጊዜ ሳናጠፋ በ እግሩ ስር ሳንገኝ በሕዝቡ ፊት ብንገኝ ጫወታ ነው አስረግጬ እናገራለሁ አንታለል እንደርሱ አይሆንም በስራው ባለቤት ፊት መገኘት መመሪያ መቀበል የግድ ነው በዚህ ዘመን ያለው ግን ሌላ ነው እግዚአብሔርን የሚፈልግና ከርሱ ሰምቶ የሚያሰማ ጠፍቷል አብዛኞቻችን በራሳችን መንገድ መድረክ በተሰጠን ቁጥር ገብቶኛል የምንለውን እንናገራለን ምናልባት የተናገርነው የሰበክነው ስህተት የሌለው የነጠር የእግዚአብሔር ቃል ሊሆን ይችላል ግን መናገሪያ መድረክ ስለተገኘ ብቻ ያገኘነውን ቃል ሳብ አድርገን መናገር አልተፈቀደም?

የስራው ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር ለህዝብህ መናገር የምትፈልገው ምንድን ነው ተብሎ ይጠየቃል ይህ ከሆነ ብቻ ነው ፍሬ ያለው አገልግሎት ማገልገል የሚቻለው።

*ከወንድም ሔኖክ ተሾመ*

*እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካልን*

በክርስትና ውስጥ ከምንም በላይ አብይ ስፍራ ያለው ምን እንደሆነ ለይቶ ማወቅ ለአማኞች ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው የክርስትናችንን ዋና ነገር ካላወቅን ዋነኛ መለያ ባህሪያችንን ልናጣ እንችላለን።ከዚህ አንጻር ከክርስትና ባህርይ ውጭ ዋነኛ ነገራቸውን ጥለው እኔ የጳውሎስ ነኝ እኔስ የአጵሎስ ነኝ እኔ የኬፋ ነኝ እኔስ የክርስቶስ ነኝ በሚል መለያየት ውስጥ ለነበሩት የቆሮንቶስ አማኞች የተጻፈላቸውን መመልከት ለሁላችንም በዚህ ዘመን ላለን ክርስቲያኖች መጣም አስፈላግጊ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ዋነኛ የክርስትና ነገር ሲገልጥላቸው አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ እኛ ግን የተስትቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን 1ኛ ቆሮ1፤22-23 ብሎ ጽፏል ይህም ቃል ክርስቲያኖች በዙሪያቸው ካለው ዓለም የሚለያቸው ን ዋና ነገር ይዟል ያም ነገር የተሰቀለውን ክርስቶስን መስበክ ነው ሃዋርያው እኝ ግን በማለት ክርስቲያኖችን ከአይሁድ እና ከግሪክ ይለያል።

ክርስቲያኖች በዚች ምድር ስንኖር ከሌሎች የሚለየን አንዱ የተሰቀለውን ህርስቶስን መስበክ መሆኑን ሁል ጊዜም ልናስተውል ይገባል አማኞች የ እግዚአብሔር ቃል ውስጥ የማይገኝ ማንነትን ለራሳችን ከመስጠት ይልቅ የክርስትና ዋና መለያ የሆነውን በአንድነት እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን ልንል ይገባል።አይሁድ ምልክትን በመለመን የታወቁ ናቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላቸው ብዙ ድንቅና ምልክትን በማድረግ ይመላለስ በነበረ ሌላ ተጨማሪ ምልክት እንዲያሳያቸው ይለምኑት ነበር ማቴ 12 ፤38 ይሁን እንጂ ለ እነዚህ ምልክት ፈላጊዎች አመንዝራትውልድ ምልክትን ይሻል ከነብዩም ከዩናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም የሚል መልስ ሰጣቸው ማቴ 12፤39 እንደ ቃሉ የሰሚዎች ልብም ሆነ የሰባኪዎች ስብከት የተሰቀለውን ክርስቶስን ማዕከል ሊያደርግ ይገባል።

በሌላ በኩል የግሪክ ሰዎች በዚህ ዓለም ጥበብ የሚታወቁ ነበሩ ግሪክም የዚህ ዓለም ጥበበኞች ተመራማሪውች ፈላስፎች በብዛት ነበሩባት ስለሆነም የብዙዎች የግሪክ ሰዎች መሻት ጥበብን ማግኘት ነበር። ሰዎች ክርስቶስ ኢየሱስ ስለአለም ሁሉ በደሌ..... ቀጣዩ ወደ ገጽ 8 ዞሯል…

*ምስክርነት … ከገጽ 4 የዞረ….*

*የጋብቻችንን ቀን ወስነን ስለነበር ወደ ሀገር ቤት ገብቼ ጋብቻችንን በዚያ ለመፈጸም በፍጹም መሄድ የማልችልባቸው ጉዳዮች (ችግሮች) ገጠሙኝ እውነት ለመናገር ነገሩ ሁሉ ከአቅሜ በላይ ሆኑብኝ በጊዜው ሁኔታዎቹ ለኔ ቀላል አልነበሩም እርሷ ግን ጸንታ በመቆም እንዳውም እኔን ታበረታታኝ ነበር ። ብዙ ችግሮች ከፊታችን አሉ ነገር ግን ጸንተህ ቁም ትለኝ ነበር ብዙ የእግ/ርን ሃሳብ ቀድማ ትረዳ ስለነበር እኔንም ለመውሰድ ብዙ አትድከም እኔ በአንተ ሳይሆን ጌታዬ እራሱ መንገድን ይከፍትልኛል በዲቪ ነው የምመጣው ትለኝ ነበር እኔ ግን በወቅቱ ነገሩ ሁሉ ጭልም ሲልብኝ ተስፋ ቆረጥኩኝ ስልክ ደውዬ በቃ ያንቺን እድል አልዝጋብሽ የተሻለ ነገር ካገኘሽ ቀጥዬ እኔም የራሴን እድል እሞክራለሁ ብዬ አልካት።*

***እውነት፦** ይህንን ድምጽ ስትስሚ ምን ተሰማሽ?*

***መቅደስ፦** በወቅቱ በጣም ያሳዝናል ምክንያቱም ይህ ሊሆን እንዳለ አስቀድሜ አውቄ ስለነበር የእግ/ር ፍቃድ እርሳ እንዳትከናወን ሁልጊዜ የሚተጋውን ክፉን ልንቃወመው ይገባል ምክንያቱም የጌታን ፈቃድ አንድ ሰው በሂወቱ ሲያገኝ ለዛ ሰው እጅግ ሰላምና እረፍት አለው እንዲሁም በጌታ ሰላምና ደስታ የተኀበኝ ሰው አምላኩን እጅግ ያከብርበታል ስለዚህ ጠላት ይህንን አይወድም ስራው ምንድነው የእግ/ር ፍቃድ ወደ ሰው እንዳይደርስ ማድረግ ነው። ስለዚህ በላይን በጣም እነግረው ነበር የጠላትን ሃሳብ እና አስተውሎ እንዲኖር ክፉን እንዲቃወም ነገር ግን አልቻለም እኔም ያዘንኩት ለዚህ ነው። ቢሆንም ግን ጌታ አሁንም ስፍራዬን እንዳለቅ ይናገረኝ ነበር።*

***እውነት፦** አንቺ የራስሽን እድል ሞክሪ እኔም የራሴን እድል ልሞክር ብለህ የወሰድከው እርምጃ ነበር?*

***በላይ፦**አዎን ነበር ጌታ ግን መንገዴን ዘጋው ጌታ ስሙ ይክበር በቃ እንዲሁ እኖራለሁ ብዬ በምልበት ሰአት አንድ ቀን ቅዳሜ ማለዳ የቤቴ ስልክ ጮህ ሳነሳው ወንድሜ ከኢትዬጵያ ነው ሰላም ካለኝ በሃላ መቅዲ ዲቪ ደረሳት አለኝ የሰማሁትን ማመን አቃተኝ ።*

***እውነት፦** ስለዚህ አጋጣሚ መቅደስ ምን ትያለሽ?*

***መቅደስ፦** ይህ አጋጣሚ አይደለም የምጠብቀው ነገር ነበር እና የሆነው ጌታን አመስገንኩ ጌታ እንደተናገረው የሚያደርግ አምላክ ነው። ዲቪ እንደወጣልኝ በማወቅ ነበር ወደ ፖስታ ቤት የሄድኩት ፖስታዬንም ይዤ ተመለስኩ ስሙ ይክበር ጌታ። ከዚያ ከወንድሙ ጋር እንገናኝ ስለነበር ደውሎ ነገረው በላይ ሲሰማ ወዲያው ደወለ እና ጌታ እንዳሳፈረው የራሱንም ደካማነት በመግለጽ ደጋግሞ ይቅርታ ጠየቀኝ እኔም ይቅርታን ከሚያውቅ ህዝብ ወገን ስለሆንኩ ይቅርታ አድርጌለት እንደገና ጀመርን ጌታ ያለውን አደረገ ምንም አይነት ወጀብ የጌታን ሃሳብ አይከለክልም እኛ ታምነን እና ጸንተን ከጠበቅነው ጌታ በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በጊዜው ይመጣል።*

***እውነት፦** ተቃርጦ የነበረው ግኑኝነታችሁ የተጀመረው ያንቺ ዲቪ በመውጣቱ ነው ማለት ነው?*

***መቅደስ፦** እኔ እንደሚገባኝ የእግ/ር ጊዜ ስለደረሰ ነው እንጂ ዲቪው ስለመጣ አይመስለኝም ምክንያቱም ዲቪውም መጥቶ አለመገናኘት ይቻል ነበር ጌታ ዲቪውን መንገድ አደረገው ጌታ ነገሮችህን ሲያይ ሁሉ ነገር እየተቻኮለ ለያገኝህ ይሻል ምክንያቱም እኔ በሂወቴ ይህን አይቻለሁ። ዲቭው በመጣልኝ በአራት ወር ውስጥ እኔ አሜሪካ ነኝ ከዚያም ጌታ ወዳየልኝ ወደዚህ ትዳር ገባሁ የአምላኬን ፍቃዱን እና ሃሳቡን ያወኩበት ደግሞም ያገኘሁት ስለሆነ አምላኬን እጅግ እጅግ አመስግነዋለሁ።*

***እውነት፦** ያሁሉ ነገር አልፎ ወደዚህ ክቡር ጋብቻ ስትገባ ምን ተሰማህ?*

***በላይ፦** እጅግ ደስታ ነው የተሰማኝ።*

***እውነት፦** ብታብራራው?*

***በላይ፦** እጅግ ነው የተደሰትኩት  ጌታን ነው የባረኩት።*

***እውነት፦** እስቲ አሁን ደግሞ በአገልግሎት ዙሪያ እንነጋገር መቅዲ በመዝሙር ጌታን ታገለጊያለሽ በሲዲ ተቀርጸ የቀረበው መዝሙርሽን ስምተነዋል በጣም ቆንጆ ነው ለሕዝብ ጆሮ ስለደረሰው መዝሙሮችሽ ጌታን እናመሰግናለን እንዴት ወደ መዝሙር አገልግሎት ልትገቢ ቻልሽ?*

***መቅደስ፦** ወደ መዝሙር አገልግሎት የገባሁት ጌታ በውስጤ የመዝሙር ጸጋን ስላኖረ ነው። ለመዘመር ቦታና ጊዜ አይከለክሉኝም ምክንያቱም በሁሉ ስፍራ ውስጤ ሲዘምር አገኘዋለሁ ።*

***እውነት፦** ብዙ ሰዎች ጸጋው እያላቸው ተገልጠው ለማገልገል መድረክ ያጣሉ ብዙ ተጽኖ ይደርስባቸዋል አንቺ አይነቱ ችግር ገጥሞሽ ያውቃል?*

***መቅደስ፦** እኔ በነበርኩበት ቤ/ክ ምንም ችግር አልገጠመኝም እንዲያውም ያበረታቱኝ ነበር።*

***እውንት፦** አገልግሎት የጀመርሽው እንዴት ነው?*

# *የትምህርት ዓምድ*

## ............ ቅብብሎሽ

*(ካለፈው እትም የቀጠለ)*

*ስለወንጌል ቅብብሎሽ ሲነሣ በዚህ ጉዳይ በጌታዋ ኃላፊነት የተሰጣትን ቤተክርስቲያንን ማስታወስ ግድ ይሆናል። በትውልድ ፍርርቆሽ መካከል የወንጌል ቅብብሎሹን በአግባቡ እንድታስኬድ የተሰጣትንም አደራ በወቅቱ እንድታደርስ በጌታ የተወከለች በመሆኗ ይኸን ተልእኮዋን ለመወጣት በታሪኳ ብዙ ውጣ ውረድ አሳልፋለች። በዚህም መሃል ጤንነቷን በሚፈታተን ችግር ውስጥም አልፋለች። እዚህ ጋ አንድ እውነት አለ። ቤተክርስቲያን ጤነኛ ካልሆነች አልፋ ትውልድን ለማከም መቸገሯ አይቀርም ።ጤንነቱ በጥያቄ ውስጥ ያለ ሰው ከሚረዳው ሃኪም ጋር ካልተገናኘ የሚደርስበት አደጋ አስከፊነት ጥያቄ እንደሌለው ሁሉ ቤተክርስቲያን ከራሷ ሃኪም፤ ከጌታዋ ጋር ካልተጣበቀች ስም አንጠልጥሎ ከመኖር ያለፈ ነገር ሊኖራት አይችልም። ይህ ደግሞ ታላቅ አደጋ ወይም ክስ ረት ነው።*

*ሐዋርያው ዮሐንስ በጌታ ታዞ ከጻፈላቸው አብያተ ክርስቲያናት አንደኛዋ የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ናት። ይህች ቤተክርስቲያን ራሷን በሚገባ ካለማወቋም በላይ እንደሚገባት ወደ ጌታዋ ባለመጠጋቷ ባላወቀችው የውስጥ ህመም ተጎድታለች። የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ራሷን የግልብጥ በማየት እውነተኛ ማንነቷን ለመገንዘብና ለመመለስ አቅም እንዳጣች ከተጻፈላት ደብዳቤ መረዳት ይቻላል።መቸም ራስን አለማወቅ ችግር ነው። የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ስለራሷ ስትናገር " ሃብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለው፤ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም " ራዕ 3፡17 በማለት ተኩራርታለች ።ሆኖም የርሷ ነገር በጌታ ሲመዘን ማንነቷ የተገላቢጦሽ ነበር። እንዲህም ተባለች፤ "……ጎስቋላና ምስኪንም ድሃም እውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ ባለጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ ተገናጸፊህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን እንድታይም አይኖችህን የምትኳለውን ኩል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ" (ራዕ 3፡18 ) ይህ አስደንጋጭም አስፈሪም ነው።*

*የሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ቢቻል ጌታዋን ቢያንስ ደግሞ አባላቶቿን ለማሳመን የምትለው ነገር ሊኖራት ይችላል። ራዕይ-መራሽ ትሁን አትሁን ግዴለም። ብቻ ራሷ ኘላን ነድፋ፤ ራሷን በራሷ መዝና በቃኝ ያሰኛት ኩራት ነበራት። ምናልባትም እንዳሁኑ ዘመን ቁሳዊ ውጤት ተኮር* (Performance Oriented) *ትሆን? ብቻ " ነጩን ልብስ " ለማየት አይኖቿ ተጋርደዋል። በጌታዋ ሚዛን ታይታ "ባለጠጋ" የተባለችው የስምርኔስ እህቷ መሆኗንም ያወቀች አይመስልም። "ስም አለህ ሞተሃል" ( ራዕ 3፡2 ) የተባለላትን ሌላ እርስዋን የምትመስለውን የሰርዴስ እህቷን ጉድ ሰምታ ይሆን ?! በተቃራኒው "ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆንም ቃሌን ጠብቀሃልና ስሜንም አልካድክምና" የተባለላትን የፊላዴልፍያን እህቷን ሚዛን ሰምታ ለመታደስ ተዘጋጅታ ይሆን?!*

*እነዚህ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት በጊዜአቸውና በትውልዳቸው መሃል የሰሩትን ሠርተው አልፈዋል። የዛሬይቱ ቤተክርስቲያን በተራዋ ምንእየሰራች ይሆን? አሁን በጌታዋ ብትመዘንስ ምን ትባል ይሆን? ጤነኛ ወንጌል ይዛ ጤነኛ ትውልድ ከማፍራት በተጨማሪ ወደሚቀጥለው ትውልድ የምታስተላልፈው ጤነኛ መልእክት በእጇ ይኖራት ይሆን? ጥያቄዎቹ አሳሳቢ ቢሆኑም የቤተክርስቲያን ራስ ጌታ ራሱ በመሆኑ ለትልውዱ አሁንም ተስፋ አለ። በተለይ የአገራችንን የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በርጋታ ስንቃኝ ከብርታት ይልቅ ድካሙ እያየለ ከመሄዱ አንፃር ቤተክርስቲያን የጌታዋን እጅ ከምንጊዜውም ይልቅ የምትፈልግበት ጊዜ ቢኖር ይኸ ዘመን ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።*

*በዚህ ጽሁፍ ለወንጌል ቅብብሎሽ ዋነኛ ሊባሉ የሚችሉ ግብአቶች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል እንዲሁም ለቤተክርስቲያን ተልእኦ እነዚህ ግብአቶች ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ በዝርዝር ለማመልከት ተሞክሯል።*

**ይቀጥላል**…………..

**ከወንድም ወርቅነህ ተስፋዬ**

**ምስክርነት** …..*ከገጽ 6 የዞረ*

**መቅደስ፦** *በውስጤ የመዝሙር ነገር እንዳለ ሳውቅ በካየር ማገልገል እንደምፈልግ ነገርካቸው የዝማሪ ጸጋው እንዳለኝ ካረጋገጡ በሃላ በካየር ሕብረት ውስጥ ገብቼ ማገልገል ጀመርኩኝ ከዚያ ለብቻዬ እንድዘምር ሕብረቱ ይገፋፉኝ ያበረታቱኝ ነበር ሁሉን ጌታ ይባርካቸው ።*

**እውነት፦** *የት ነበር የምታገለግይው?*

**መቅደስ፦** *በመጀመሪያ አገልግሎት የጀመርኩት በሐረር ከተማ ሲሆን ከዚያም ስራ ይዤ ወደ ድሬዳዋ ሄድኩኝ በዚያም ቀጠልኩኝ ።*

**እውነት፦** *ወንድም በላይ አንተስ ስለአገልግሎት ምን የምትለው አለህ?*

**በላይ፦** *እኔ ብዙ የምለው የለኝም ሆኖም ወደ እዚች ምድር ከመጣሁ ወደ አስራ አምስት አመት አካባቢ ሊሆነኝ ነው ታዲያ በዚህ ሁሉ አመት ከጌታ ቤት ከማእዱ ዙሪያ አልታጣሁም በከፍታም በዝቅታም አገለግላለሁ ጌታን ስለዚህ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።*

**እውነት፦** *በምን የአገልግሎት ዘርፍ ነው የምታገለግለው?*

**በላይ፦** *በመጀመሪያ በጸሎት አገለግል ነበር በኋላ ግን በእኔም ውስጥ የዝማሬ ነገር ሲታይ ይህን የሚያዩ ሰዎች በጸጋዬ እንድቆም ይገፋፉኝ ስለነበር ወደ ዝማሬ አገልግሎት ገብቻለሁ አሁን የማገለግለው በካየር ውስጥ በህብረትና በግል ሶሎ አገለግላለው።*

**እውነት፦** *መቅዲ አገልግሎት በአሜሪካ እንዴት ነው?*

**መቅደስ፦** *እንደምታየው ነው……..*

**እውነት፦***ልዩነት አለው ከሀገር ቤቱ ጋር የገጠሙሽ ችግሮችስአሉ?*

*መቅደስ፦ ይሄ ነው የምለው ነገር የለም ምናልባት ብዙ የአገልግሎት መድረክ ስለሌለ ልዩነቱን ማወቅ አልቻልኩም ።*

***እውነት፦*** *ቁጥር አንድ የመዝሙር ሲዲሽን አገር ቤት ለነበርሽበት ቤ/ክ እዚህ ደግሞ ላለሽባት ቤ/ክ ለህንጻ ግዥ እንዲሆን ስጥተሻል ይህን ለማድረግ ምን አነሳሳሽ?*

***መቅደስ፦*** *የምቀበላቸው መዝሙሮች ፈጽሞ የእኔ አይደሉም የጌታ ናቸው በነጻ የተቀበልኩትን በነጻ ሰጠሁኝ ምክንያቴ ይሄ ነው ወደፊትም ቢሆን አላማዬ ይሄ ነው።*

***እውነት፦*** *ቁጥር ሁለት ሲዲ ለማውጣት አላሰብሽም?*

***መቅደስ፦*** *አስባለሁ እየጸለይኩኝ ነው።*

***እውነት፦*** *በመጨረሻ ማስተላለፍ የምትፈልጉት መልክት ካለ?*

***ሁለቱም፦*** *እኛ በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ አልፈን አንድ እውነት ተምረናል ይህም ጌታን በነገር ሁሉ በእምነትና በጽናት መጠበቅ ትልቅ በረከት እንደሆነ ነው የተረዳነው በእርግጥ መታገስ ከባድ ነው ነገር ግን ፍሬው እጅግ ይጣፍጣል እና ሁላችን በነገር ሁሉ በጽናት ጌታን መጠበቅ ብንችል መልካም በረከቱን ከጌታ እጅ እንቀበላለን ይህን ነው የምንለው።*

***እውነት፦*** *ስለሰጣችሁን ሰፊ የህይወት ምስልርነት ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ እናመሰግናለን።*

## ሕዝብ ይረፍባችሁ

ድምጼን እያሰማሁ ልጩህ ስለመንጋው
እረኛው በትኖት ለተቅበዘበዘው
በአገልግሎት ሰበብ ትቶት ለነጎደው
        ዕድል ሰጠኝ ጌታ ወጣ ብዬ ልስበክ
        አውሮፓ ያሉትን በወንጌል ልማርክ
ደግሞ በሳምንቴ ሂጄ አሜሪካ
ከቃሉ በረከት ሕዝቡን በዚያ ላርካ
እየዞርኩ ላገልግል በተሰጠኝ ጸጋ
        እያለ ሲባዝን ም ዕራብን ሲያካልል
        የራሱን መንጋ ጥሎ ለሌላው አለሁ ሲል
ጥበቃውን ለሚሻ በጉ ግድ ከሌለው
እረኛ መባሉ ታዲያ ምኑ ላይ ነው
ካልሁባት ቤተ ክርስቲያን ከሙሉ ጉባዔ
ተቀበሉ ይላል ይኸው ሰላምታዬ
        እረኛ ነኝ ብሎ ሰይሞ እራሱን
        ካሉት ም ዕመናን አያውቅም አስሩን
        ግማሹም አልሰሙም ም ዕራብ መንጎዱን
ታዲያ የቱን ሰላምታ ነው የምንቀበለው
ጉባዔው ተስማምቶ መደዚህ ሳይልከው
የጌታን ቃል መንገር ልቡን ካነሳሳው
ብዙ ሕዝብ አለኮ ወንጌል ያልደረሰው
መንገድ ሳያበዛ ባቅራቢያው የሚያገኘው
በአመት አራቷን ወር በቤቱ እየኖረ
እርሱ ግን በድፍረት እረኛ ነኝ እያለ
መንጋው ግን አልቻለም ድምጹን እንኳን መስማት
መቅበዝበዝ ነው እጣው ስለሌለው ምሪት
የ እረኝነት ትርጉም እኔ እንደገባኝ
        ጌታችን በቃሉ እንደገለጸልን
        ስለበጎቹ ሲል መስጠት ነው እራስን
በጎቹም ያውቁታል እርሱም ያውቃቸዋል
ድምጹን እይሰሙ አምነው ይከተሉታል
ግን ይህ መተዋወቅ ከሌለ በእነርሱ
እርሱም አያውቃቸው አያውቁት እነርሱ
        ተኩላም ሊያጠቃ ቢመጣ ከመንጋው
        አይቀርም እረኛው መገስገስ ትቷቸው
ስለዚህ እረኞች መንጋችሁን ጠብቁ
ጠላትን ለማጥቃት በእውነት ታጠቁ
ደግሞም ለየበጉ በግዜው ተገኙ
የእግዚአብሄር ምስጢር መጋቢዎች ናችሁ
በአገልግሎታችሁ ታማኞች ሆናችሁ
መቅበዝበዙን ትቶ ህዝብ ይረፍባችሁ።

**በእህት ሳባ ተስፋዬ**

### *ከገጽ 5 የዞረ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን....*

**በመስቀል ላይ የመሞቱን ዜና እንደ ሞኝነት ይቆጥሩታል ነገር ግን የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ቢሆንም ለእኛ ለምናምነው ግን የ እግዚአብሔር ኀይል ነው 1ኛ ቆሮ1፤18 በዚህም እግዚአብሔር የዚህችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አድርጓል1ቆሮ1ል20 በመሆኑም ክርስቲያኖች የተሰቀለውን ክርስቶስን ልንሰብከው ይገባል የተሰቀለውን መስበክን ይህል ለሰባኪው ውጤት የሚያመጣ ተሰባኪውንም ወደመዳን የሚያደርስ ምልክትም ሆነ ጥበብ የለም.። ይህ ያለንበት ዘመን እንደ አይሁድ ምልክት ፈላጊዎችና እንደ ግሪክሰዎች የዚህን ዓለም ጥበብ የሚከታተሉ ሰዎች የበዙበት ዘመን ነው በዙሪያችን በሚገኙ በ እነዚህ ሁሉ ሰዎች መካከል እኛ ክርስቲያኖች የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን እርሱ ሃጢያታችንን በመስቀል ላይ ተሸክሞ ስለሁላችን ሲሞት እንዳላፈረብን ሁሉ እኛም አናፍርበትም ብናፍርበት ደግሞ እርሱ በክብሩ ዳግመኛ ሲመጣ ያፍርበናል ሉቃስ 9፤26 ስለሆነም ክርስቶስን ከስቅላቱ ጋር በወንጌል ቃል ስንሰብክ በምንም አናፍርምና ሮሜ 1፤16 እኛ አማኞች ከተጠራንባችውና ከተለየንባቸው ዓላማዎች አንዱ ክርስቶስን ለማያውቁ ከ እግዚአብሔር ርቀው ለሚጠፋው ለዚህ ዓለም እንደ ግሪኮች ጥበብን ለሚሹና ለሚከተሉ እንደ አይሁድም ምልክትን ለሚለምኑ በ ዓለም ሳሉ ላላመኑ ጌታ ኢየሱስን እንደግል አዳኛቸው አድርገው ላልተቀበሉ ሁሉ የተሰቀለውን ክርስቶስን በኑሮም በቃልም መስበክ ነው።**

**በወንድም አባቡ**